# ለምን አይሙት ድሃ?

(አብርሃም በየነ፣ ነሃሴ 2001)

በሰው ህይዎት ፍጠረት - ሞት እንዳለ ሁሉ፣
በሞትም ውስጥ ህይዎት - አለበት ፀበሉ፣
ስለዚህ የሰው ልጅ - ከሞተ በሁዋላም፣
በህይዎት እንዲኖር - በነፃነት ሰላም፣
ቁምነገር ያለበት - ይሙት ሥራ ሠርቶ፣
ከዚህ ዓለም ይለይ - ድህነቱን ከልቶ።

ድህነት በቁሙ - ነቀዝ እየፈጀው፣
ለምን አይሙት ድሃ - መኖር ምን ሊበጀው?
መኖር ምን ሊበጀው - በመኖር አምሃ፣
ሙቶ ይገላገል - ለምን አይሙት ድሃ?
ድሃ ይሙት ይብቃው - ሀብታሙ ይቀጣ፣
ከበዝባዥ ከጨቋኝ - በሞት ነፃ ይውጣ።

ግቢ ነፍስ ውጪ ነፍስ - በድህነት ታንቆ፣
ለምን ይኑር ድሃ - ምን ተስፋ ሰንቆ?
ለምን ድሃ ይኑር - እየተኮነነ፣
በማጣቱ ሃጢአት - እየተደየነ፣
ከሃብቱ ሃብት የለው - ከመብት ስብዕና፣
ድሃ ለምን ይኑር - ለምንስ እርባና፣
ለምን ይኑር ድሃ - ሲገዛ ዕድሜልኩን፣
ይሙት አሳምሮ - በሞት አጥቦ መልኩን፣
በሞት ህይዎት ይውለድ - አፈር ላይ ተኝቶ፣
እንደ አዝዕርት ጥሬ - ድሃ ይብቀል ሙቶ።

ለሃብታም ካልሆነ - ለገዥ መደብ ጌታ፣
ድሃ ይኑር ማለት - ለማን አዘኔታ፣
ሀብታሙ በድሎት - እንዲኖር ዘምኖ፣
ድሃ ለምን ይኑር - ድህነት ተጭኖ?
ከሞት ጋር ተዋግቶ - በዱር በሸለቆ፣
እናም ይሙት ድሃ - ድህነቱን አውቆ።

ስልጣኑን ድሎቱን - ፍስሃውን ጥሎ፣
ሃብታም ለምን ይሙት - ምን አተርፍ ብሎ?
ድሃ ይሙት እንጂ - ሁሉን አጠቃሎ፣
እንደ ድህነቱ - ድሃ ይሙት በቃው፣
የባርነት ቀንበር - ይወገድ ከጫንቃው።

ሃብታም ያለ ድሃ - መኖር እንደማይችል፣
ከተኛበት ይንቃ - በሞት ጩኸት ቃጭል፣
በግፍ አፈላማ - ሃብተሙን አስይዞ፣
ድሃ ካገር ይጥፋ - ድህነቱን ይዞ፣
ድህነቱን ይዞ - ዱር ይግባ በርሃ፣
ነፃነቱን ያውጅ - በቃው ይሙት ድሃ።